

# የመክሊቶቹ ታሪክ

- አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንድ ነገር ማስተማር ሲፈልግ ታሪክን ይናገር ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የመክሊቶቹን ታሪክ እስኪ እንየው።

- አንድ ቀን አንድ ሰው ራቅ ወዳለ ስፍራ ይጓዝ ነበር። በሚሄድበት ጊዜም አገልጋዮቹ ባለው ንብረትና ሀብት ላይ አደራ እንዲረከቡ ፈለገ። ስለዚህም ወደእርሱ ጠራቸው።

- ለመጀመሪያው አገልጋይ 5 መክሊቶችን ሰጠው። መክሊት ሳንቲም አልነበረም። እንደብር ውድ የሆነ ማእድን ነበር።

- ይህ ሰውም ወዲያውኑ መስራት ጀመረና መክሊቱን 2 እጥፍ አደረገው። ስለዚህ አሁን በእጁ 5 መክሊት ሳይሆን 10 መክሊት ነበረው።

- ጌታው ለሁለተኛው አገልጋዩ 2 መክሊት ሰጠው። ምናልባትም ጌታው ይህን የሚያህል መክሊት የሰጠው ከዚህ በላይ ኃላፊነት አይሸከምም ብሎ ስላመነ ይሆናል። ሁለተኛውም አገልጋይ ተሳካለትና መክሊቱን እጥፍ አደረገው ። በ2 መክሊት ጀምሮ አሁን 4 መክሊት አለው።

- ሶስተኛው አገልጋይ እንደመጀመሪያዎቹ ሁለት አገልጋዮች አልተሳካለትም። ጌታው በሚገባ አደራውን ይወጣል ብሎ ስላመነ አንድ መክሊት ብቻ ሰጠው። እርሱም መክሊቱን እንደሌሎቹ መጨመር ይችል ነበር። በዚህ ምትክ ያደረገው ነገር መሬት ቆፍሮ እንዲያተርፍበት የተሰጠውን መክሊት መቅበር ነበር።

- አምስት መኪሊት የተቀበለው ሰው መክሊቶቹን ይዞ መጣና ለጌታው እስካተረፈው ተጨማሪ አምስት መክሊት ጋር አስረከበው። ለጌታው ይህን በማሳየቱም ደስተኛ ነበር።

- ጌታውም በዚህ አገልጋይ እጅግ ተደሰተ። እንዲህም አለው፣ "መልካምና ታማኝ ባሪያ ነህ። በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ አግኝቼሃለሁ። ስለዚህም ተጨማሪ ኃላፊነት እሰጥሃለሁ። ስለዚህ ና ከእኔ ጋራ ደስታዬን ተካፈልልኝ!" አለው።

- በመቀጠልም 2 መክሊት የተሰጠው ሌላኛው አገልጋይ መጣ። እርሱም የተሰጠውን መክሊት እጥፍ አድርጎ እንዳተረፈ ጌታው አየ። ስለዚህም ልክ አስር መክሊት ይዞ በጌታው ፊት እንደቀረበው ባሪያ ይኸኛው ባሪያም ተመሳሳይ የሙገሳ ቃላትን ከጌታው ተቀበለ።

- አንድ መክሊት ተቀብሎ የነበረው ባሪያ ግን በመሬት ውስጥ ቀብሯት የነበረውን መክሊት ከቀበረበት አውጥቶ ወደ ጌታው ይዞ መጣ። ጌታውንም እጅግ ጨካኝ እንደሆነ ከከሰው በኋላ ለእርሱ ተቀጥሮ መስራቱ ስህተት እንደሆነ ተናገረ። በዚህ ምክንያትም ጌታውን ፈርቶ መክሊቱን መሬት ውስጥ እንደቀበረ ገለፀለት። በመጨረሻም፣ "የሰጠኸኝ መክሊት ይኸውና!" ብሎ ሰጠው።

- በዚህ ባሪያ ላይ እጅግ የተቆጣው ጌታም ይህንን ባሪያ እጅግ ክፉና ሰነፍ ባሪያ ነው አለው። እርሱ ራሱ ነግዶ ማትረፍ ባይችል እንኳን ለአትራፊዎች ሰጥቶ ወለዱን (ትርፉን) ማቆየት ይችል እንደነበር ጌታው ነገረው። (አይሁዳውያን ከወገኖቻቸው ማለትም ከሌሎች አይሁዳውያን ላይ ወለድ ወይንም ትርፍ መቀበልን ሕጉ አይፈቅድላቸውም ነበር። ሆኖም አይሁዳዊ ላልሆነ ሰው በወለድ ማበደር ይችሉ ነበር።)

- ከዚያም ጌታው አንዷን መክሊት ወስዶ አስር መክሊት ላለው አገልጋይ ሰጠው። ባለአንድ መክሊቱ ባሪያም የጌታውን አደራ በአግባቡ ስላልተወጣ ተቀጣ።

- ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን፡ እግዚአብሔር የሰጠንን ማንኛውንም "መክሊት" ልንጠቀምበት ይገባል። ገንዘብ፣ ችሎታ፣ ወይንም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። በማስተዋል ከተጠቀምንበት እግዚአብሔር ይጨምርልናል። ደግሞም ለእርሱ ብዙ ክብር ይሆናል።

*የመክሊቶቹ ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 25፡ 14 – 30 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com